Palliative Care Victoria

# የማስታገሻ እንክብካቤ ምንድን ነው?

## What is Palliative Care?

የማስታገሻ/Palliative እንክብካቤ የማያገግም በሽታ ላለባቸው ሰዎች የሚሰጥ የጤና እንክብካቤ ነው። ለታካሚዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ምቾት ድጋፍ እና የህይወት ጥራት ላይ ያተኩራል። ሰዎች የቻሉትን ያህል ለቻሉት ጊዜ እንዲኖሩ ይረዳቸዋል።

Palliative care is health care for people living with a terminal illness. It focuses on comfort, support, and quality of life for patients and their families. It helps people live as well as they can for as long as they can.

### የማስታገሻ እንብካቤ መቼ ሊጀምር ይችላል?

የማስታገሻ እንክብካቤ በመጨረሻዎቹ ሳምንታት ወይም ቀናት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ህመም ሲኖር ሊጀምር ይችላል። በብዙ አጋጣሚዎች አንድ ሰው ለሕመሙ ሌሎች ሕክምናዎችን በሚወስድበት ጊዜ የማስታገሻ እንክብካቤ ሊያገኝ ይችላል።

### When can palliative care start?

Palliative care can start at any time of a progressive illness, not just in the final weeks or days. In many cases, a person can receive palliative care while they are still receiving other treatments for their illness.

## የማስታገሻ እንክብካቤ የሚሰጠው ማነው?

የማስታገሻ እንክብካቤ በማንኛውም የጤና ባለሙያ እንደ አጠቃላይ ሐኪም፣ የህክምና ባለሙያ ወይም ነርስ ሊሰጥ ይችላል።

የአንድ ሰው ምልክቶች ይበልጥ ውስብስብ በሚሆኑበት ጊዜ ልዩ ወይም ስፔሻሊስት የማስታገሻ የእንክብካቤ አገልግሎቶች ሊሰጡ ይችላሉ።  ብዙውን ጊዜ የሚመሩት እንደ ጠንካራ ህመም፣ ማስታወክ እና የመተንፈስ ችግር ያሉ የህይወት መጨረሻ ምልክቶችን በመቆጣጠር ላይ በተካነ ዶክተር ወይም ነርስ ነው።

የስፔሻሊስት የማስታገሻ እንክብካቤ ቡድን ከአንድ ሰው ነባር የጤና እንክብካቤ ቡድን ጋር በመተባበር መስራቱን ይቀጥላል እና የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል:-

- ዶክተሮች
- ነርሶች
- የተባበሩ የጤና ባለሙያዎች
- ፋርማሲስቶች
- የሥነ ልቦና ባለሙያዎች
- መንፈሳዊ ወይም የመንፈሳዊ እንክብካቤ ሰራተኞች
- የማስታገሻ እንክብካቤ በጎ ፈቃደኞች

## ልዩ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዴት ማግኘት ይቻላል?

ወደ ልዩ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶች ሪፈራል በግለሰብ ወይም በቤተሰብ አባል ወይም ተንከባካቢ ወይም በማንኛውም የጤና ባለሙያ ሊደረግ ይችላል።



## Who provides palliative care?

Palliative care can be provided by any health professional such as a general practitioner, medical specialist or nurse.

Specialist palliative care services can be involved when a person's symptoms become more complex. They are usually led by a doctor or a nurse who specialises in controlling end of life symptoms such as strong pain, vomiting and difficulty in breathing.

A specialist palliative care team will continue to work in partnership with a person's existing healthcare team and may include:

- Doctors
- Nurses
- Allied health professionals
- Pharmacists
- Psychologists
- Spiritual or pastoral care workers
- Palliative care volunteers

## How to get specialist palliative care services?

A referral to specialist palliative care services can be made by an individual or family member or carer, or any health professional.

## ልዩ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶች ምን ዓይነት እንክብካቤ ይሰጣሉ?

ልዩ ማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- ውስብስብ አካላዊ የህመም ምልክቶችን ለመቆጣጠር ይረዳል
- በማህበራዊ፣ ባህላዊ እና መንፈሳዊ ጉዳዮች ጋር የተገናኘ ድጋፍ ይሰጣል
- ለበሽተኛው እና ለቤተሰቦቻቸው ወይም ለተንከባካቢዎቻቸው የምክር እና የሀዘን ድጋፍ ይሰጣል

## What care do specialist palliative care services provide?

Specialist palliative care services include:

- Help controlling complex physical symptoms
- Support with social, cultural and spiritual concerns
- Counselling and grief support for the person and their family or carers

## ልዩ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶች የት ሊሰጡ ይችላሉ?

የማስታገሻ እንክብካቤ በነዚህ ስፍራዎች ሊሰጥ ይችላል:-

- ቤት ውስጥ
- ሆስፒታል ውስጥ
- በማገገምያ ውስጥ
- በአረጋውያን የእንክብካቤ መኖሪያ ቤት ውስጥ
- በሚደገፍ የአካል ጉዳተኞች ማረፊያ ውስጥ

## Where can specialist palliative care services be provided?

Palliative care can be provided:

- At home
- In hospital
- In a hospice
- In a residential aged care home
- In supported disability accommodation

## ልዩ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶች ምን ያህል ያስከፍላሉ?

አብዛኛዎቹ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶች ነፃ ናቸው። አስፈላጊ ከሆነ ከእርስዎ ጋር የምንወያይባቸው የመድኃኒቶች ወይም የመሳሪያዎች አንዳንድ ወጪዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

## How much do specialist palliative care services cost?

Most palliative care services are free. There may be some costs for medicines or equipment which will be discussed if required.

## ለቤተሰብ እና ለተንከባካቢዎች ምን ዓይነት ድጋፍ አለ?

ልዩ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎቶች ለቤተሰቦች እና ተንከባካቢዎች ተግባራዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ ይሰጣሉ።

## What support is available for family and carers?

Specialist palliative care services also provide practical and emotional support for families and carers.

## አስተርጓሚ ቢያስፈልግስ?

ሲመጡ አስተርጓሚ እንደሚያስፈልግ ለአገልግሎቱ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

## እንዴት አገልግሎት ማግኘት እችላለሁ ወይም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እችላለሁ?

- ሐኪምዎን፥ ልዩ ባለሙያተኛዎን ወይም ማንኛውንም የጤና ባለሙያ ያነጋግሩ
- ወደ የአካባቢዎ የማስታገሻ እንክብካቤ አገልግሎት ይደውሉ
- የቪክቶሪያ የማስታገሻ እንክብካቤን (Palliative Care Victoria) ያነጋግሩ
  - » ስልክ ቁጥር 03 9962 9644 (ከጠዋቱ 9 ሰዓት እስከ ምሽቱ 5 ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ አርብ)
  - » ኢሜይል፡- info@pallcarevic.asn.au
  - » ድህረ ገጹን ይጎብኙ - https://www.pallcarevic.asn.au/

Interpreter

የስልክ አስተርጓሚ ማዘጋጀት ይቻላል። እባክዎን የትኛውን ቋንቋ እንደሚፈልጉ ይንገሩን?



## What if an interpreter is needed?

It is important to let the service know if an interpreter is needed for a visit.

## How do I find a service or get more information?

- Talk to your doctor, specialist or any health professional
- Call your local Palliative Care Service
- Contact Palliative Care Victoria
  - » Telephone 03 9962 9644 (9am to 5pm, Monday to Friday)
  - » Email: info@pallcarevic.asn.au
  - » Visit the website: https://www.pallcarevic.asn.au/

Interpreter

A telephone interpreter can be arranged. Please tell us what language you need.

**Palliative Care**
Victoria

# የማስታገሻ እንክብካቤ ምንድን ነው?

Amharic

የእኛን ድረ-ገፅ ለማየት ስካን ያድርጉ

Scan to view our website